# የሽረት ሽረት

አብርሃም በየነ

ባባቶቻችን ዘመን የዕምነት አንደበት

ቃል ማተብ ነበረው የሚታመንበት

እንደዛሬው ሳይሆን ዕምነት ተካክዶ

ትከሻ ያጎብጣል ቃል ከሸክም ከብዶ

ያለ እማኝ ወረቀት ሰው ቆሞ በቃሉ

ፀሀይ ይሞቅ ነበር ያለ ፊርማ ውሉ

ባባቶቻችን ዘመን ድሮ ጥንት ድሮ

ፊርማና ወረቀት እንደ ውል ቋጠሮ

በሰዎች ህሊና

ሳያገኙ ዕውቅና

አባቶቻችን ቃል ማተብ ነው ሲሉ

እምነቱ ነበር ለሁሉም ፊርማው ቃሉ

ቃል ማተብ ነበረ ብለናል ባባቶቻችን ዕድሜ

በዚህ ባንተው ዘመን ግን ወንድሜ

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ቃል ተከዳድቶ

እስላም አንገቱን ነው ማተቡን ፈትቶ።

……….. …………

በዘር ማበላለጥ ነጭ ከጥቁር ቢጫ

በመደብ ልዩነት በሀብት ብላጫ

በወንድና በሴት ትልቅና ትንሽ

በፆታ ማስመሪያ የልዩነት ቀለም

መድሎና ልቅና በሚዳኙት ዓለም

እንደ ሞት ማን አለ ፍትህን አቅልሎ

አፈር ላይ ያኖረ ሰውን አስተካክሎ።

........... .............

ጊዜን ጊዜ ሽሮት ብድሩን መልሶ

ያለቀሰው ሲስቅ የሳቀው አልቅሶ

ቂም በቀሉን ሲቀብር ክንድ ጉድጓድ ምሶ

ይገዛን ይሆናል ያኔ ፍቅር ነግሶ።

የካቲት 2005

............ ............